**ሳምንታዊ ዜና (ሰኔ 21 ቀን 2000 ዓ. ም.)**

**ረሀቡ እየተስፋፋ መሆኑ ተጋለጠ፣ በወሎ በርካታ ወረዳዎች የረሀቡ ሠለባ ሆነዋል፣በአለም ላይ ከፍተኛ የኑሮ ውድነት ያለው በኢትዮጵያ ነው ሲል የመንግስታቱ ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች መግለጫ አወጣ፣የእድር ገንዘቦች ለሽማቾች ማህበር ገቢ ይደረግ ተብሎ በግዳጅ ትዕዛዝ ወጣ፣ በሚሌ አካባቢ ታጣቂዎች በሰነዘሩት ድንገተኛ ጥቃት በወያኔ ጦር ላይ ከባድ ጉዳት ደረሰ፣ ለሰዓታት የጅቡቲ መንገድ ተዘግቶ ዋለ፣ በርካታ ሰራተኞች ከስራ ሊባረሩ መሆኑ ተጋለጠ፣ ሁለት ከፍተኛ የወያኔ ካድሬዎች ስርዓቱን ከድተው እንግሊዝ ጥገኝነት ጠየቁ »»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»»**

**ከፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ሬዲዮ ሌላም ዜና በዝርዝር ያንብቡ…………………………..**

የኑሮ ውድነቱና ረሀቡ ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ መሆኑን አለም አቀፍ ድርጅቶች ገለፁ::

በሀገሪቱ በተከሰተው ረሀብና የኑሮ ውድነት ሳቢያ በየቀኑ ዜጎች እንደጠቅል እየረገፉ ባለበት በዚህ ወቅት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ችግሩ ስር የሰደደ መሆኑን እና በቅርቡ ክረምቱ ላይ ደግሞ ከዚህ የከፋ እንደሚሆን ስጋቱን ባወጣው መግለጫ አስታወቀ::

የአለም ምግብ ፕሮግራም በበኩሉ የኑሮ ውድነቱ ከአለም ዋጋ ጋር በጭራሽ እንደማይገናኝና በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተው የኑሮ ውድነት እጅግ የከፋ መሆኑን ገልፆ አስቸኳዩ ድጋፍ ካልተደረገ የከፋ አደጋ ሊከሰት እንደሚችል ስጋቱን ገልጿል::

ገበሬው ትርፍ አምራች ሆኗል እያሉ የወያኔው መሪዎች መለስን ጨምሮ ካድሬዎቹ ሲለፍፉ እንዳልነበር ዛሬ ረሀቡ አፍጥጦና አግጥጦ ሲመጣ የውሸታቸው ድሪቶ በመጋለጡ የተበሳጩት እነዚሁ ቡድኖች በተለይ በደቡብ እና በሐረር የተከሰተው ረሀብ ወደ አማራ ክልል መዛመቱንም ድርጅቱ ገልጿል::

በደቡብና በሰሜን ወሎ 18 ወረዳዎች እስከዛሬ ድረስ ለሕፃናት ተጨማሪ ምግብ እርዳታ ሲሰጥ የነበረ ቢሆንም በአሁን ሰዓት እርዳታው ያነሰ በመሆኑ 7 ወረዳዎች ብቻ እንዲሰጡ በመደረጉ የሰው ችግር እየተስፋፋና እየጠነከረ መምጣቱን የገለፀው ይኸው ድርጅት በተለይ በክረምቱ ወራት ከፍተኛ እልቂት ሊኖር እንደሚችልም አስገንዝቧል::

ገበሬው የሌለውንና ያላመረተውን አምርቷል እያሉ የሚለፍፉት የወያኔ ባለሥልጣናት ረሀቡ ዜጎችን እንደቅጠል እያረገፈ ባለበት በዚህ ወቅት እንኳዋን ምንም ሳይመስላቸው በሚፈነጩበት ቴሌቭዥን «የግንቦት 20 የህዝብ በዓል ነው» እያሉ የሕዝብ ጆሮ እያደነቆሩ ሲሆን፣ እውነታውን ባጋለጡ አለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ መልሰው የስም ማጥፋት ዘመቻ መጀመራቸውም ታውቋል::

በወሎ ውስጥ ሳይንት፣ ለጋምቤ፣ ደሴ ዙሪያ፣ ጉባ ላፍቶ እና ዋድላ ደላንታ ወረዳዎች የዚሁ የረሀቡ ተጠቂ ቦታዎች መሆኑን የገለፀው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብአዊ ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ ሁኔታው በዚሁ ከቀጠለ አሳሳቢ መሆኑን ገልጿል::

በሐረር በአርሲና በደቡብ ኢትዮጵያ የጀመረው ረሀብ ወደ አማራ ክልል ተሸጋግሮ የቀጠለ ሲሆን በአሁን ሰዓት በሀገሪቱ የተከሰተው ረሀብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ከፍተኛ እንደሆነ ወደፊትም በቀጣይነት አስጊ መሆኑን አለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች እየገለፁ ባለበት ወቅት ወያኔ ለዜጐቹ ካለው ንቀትና ጥላቻ የተነሳ የወሰደው አንዳችም እርምጃ የሌለ መሆኑም ታውቋል::

በሀገርና በህዝብ ላይ ለ17 ዓመታት ሲቀልድ የኖረው ወያኔ ገበሬውን ትርፍ አምራች ሆኗል እያለ ለጋሽ ድርጅቶች በችግሩ ጊዜ እንዳይደርሱለት እየሸፈነ በአጭሩ ሊቀጭ የሚችለውን ችግር ስር እስኪሰድ ድረስ አፍኖ ማቆየቱ ሳያንሰው አሁንም ረሀብተኛ ቁጥሩ አነስተኛ ነው እያለ አሳፋሪ መግለጫ መስጠቱ የአለምን ሕብረተሰብ ያስገረመ ነው ሲሉም የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እየገለፁ ናቸው::

በኢትዮጵያ ከተከሰተው ረሀብ በተጨማሪ የኑሮ ውድነቱ ከአለም ምግብ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር እጅግ ከፍተኛ እና በጣም ውድ መሆኑን ያረጋገጡት የአለም ምግብ ድርጅትና ለጋሽ ድርጅቶች ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባው ስንዴ በኩንታል 350 ብር ሲሆን በሀገር ውስጥ የተመረተው ስንዴ ግን ከ600 መቶ ብር በላይ መሆኑን ገልጿል::

ወያኔ የስልጣን እድሜዬን አራዝማለሁ በሚል የሀገሪቱን አንጡራ ሀብት ለመሣሪያ መግዣና ለወታደራዊ ተቋም ማስፋፊያ እያዋለው ከመሆኑም በተጨማሪ የተረፈውንም ባለስልጣናቱ እየተከፋፈሉ ሀገርንና ህዝብን በድህነት አረንቋ ውስጥ ከተውታል ያሉት አንድ የኢኮኖሚ ባለሙያ ስንዴ በርካሽ ዋጋ ገዝቶ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት እየቻለ ዜጐች በረሀብና በኑሮ ውድነት ሲያልቁ ዝም ብሎ መመልከቱ የቡድኑን አረመኔነት የሚያሳይ ነው ሲሉም በቁጭትና በእልህ ይገልፃሉ::

ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ የአንድ ኩንታል ጤፍ ዋጋ ከ1300 ብር በላይ እየተሸጠ ባለበት በዚህ ወቅት የ1 ኩንታል በቆሎ ዋጋ 600 ብር በሆነበት የወያኔው ቡድን በአለም ገበያ ላይ በርካሽ ስንዴ ገዝቶ ማስመጣት እየቻለ ሕዝቡን በረሀብና በችጋር እየጠበሰ መገኘቱ አሳዛኝ ነው ያሉት አንድ የባንክ ባለሙያ በሀገሪቱ ውስጥ ምንም አይነት የውጭ ምንዛሬ ባለመኖሩም ነጋዴዎች እንኩዋን እንዳያስገቡ ተቸግረው ያሉበት ወቅት ነው ሲሉ ይገልፃሉ::

በአሁን ሰዓት የምግብ ዋጋ ንረቱ በሌሎች የአለም ሀገራት የተከሰተ ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን የተከሰተው የምግብ ዋጋ ማሻቀብ ከአለም ሀገራት በእጅጉ የተለየና በጣም ውድና ህዝብ ከሚገዛው አቅም በላይ በመሆኑ ህዝቡ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት የተዳረገ መሆኑን አለም አቀፍ ድርጅቶች ገልፀው ከአሁኑ ይልቅ የክረምቱ ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑንም ስጋታቸውን እየገለፁ ይገኛሉ::

የወያኔው ቡድን አንዱ ረሀብ አልተከሰተም እያለ ሲዋሽ ቆይቶ እውነታው ሲረጋገጥ እንደገና የተራቡት ሰዎች ቁጥራቸው አነስተኛ ነው። በቁጥጥራችን ስር እናውላለን እያሉ በህዝብ ሕይወት ሲቀልዱ እንደነበር ያስታወሱት አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ ዛሬ ረሀቡ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተስፋፍቶ ያለበት ጊዜ ሲሆን የኑሮ ውድነቱም ከአለም በላይ የናረበት ደረጃ ላይ ተደርሷል ሲሉ ገልፀዋል።

አክለውም ወያኔ ለራሱ እንዲያመቸው የሽማቾች ማህበር ይቋቋም ብሎ በአዲሱ ለገሰ የሚመራ ቡድን ተቋቁሞ በየከተማውና በየቦታው የሽማቾች ማህበር እያቋቋመ ለፖለቲካ መጠቀሚያ እያዋለው ከመሆኑም ባሻገር ለችግር ጊዜ መርጃ ይሆናሉ ተብለው የተቋቋሙት እድሮችም ያላቸውን ገንዘብ ወደ ሽማቾች ማህበር እንዲያስገቡ ትዕዛዝ መሰጠቱም ያሳዝናል ሲሉ እንባ እየተናነቃቸው ይገልፃሉ።

ሀገር እናስተዳድራለን ብሎ መንበረ ስልጣኑን በግድ የያዘው ወያኔ በሀገሪቷ ሕዝቦች ላይ የተከሰተውን የኑሮ ውድኑት ለማርገብ የራሱን ሚና መጫወት ሲገባው ሕዝቡ ለችግር ጊዜ ይሆነኛል ብሎ ለመረዳጃ ያስቀመጠውን የእድር ገንዘብ ለሽማቾች ማህበር በግዳጅ ገንዘቡን ገቢ እንዲያደርጉ መታዘዙ ያሳዝናል ሲሉም እኚሁ አዛውንት ይገልፃሉ።

የወያኔ ባለሥልጣናት ልጆቻቸውን ወደ ውጭ ሀገር ልከው በኢትዮጵያ ህዝብ ገንዘብ አንደልባቸው እያዝናኗቸው ሲሆን፣ ሕዝቡ የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ በከፍተኛ የኑሮ ውድነት ውስጥ መግባቱ ሳያንሰው ለዘመናት ሲያጠራቅም የነበረውን ገንዘብ መውሰዱ ያሳዝናል፣ ያበግናል ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በቁጭት ይገልፃሉ።

ረሀቡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች እየተስፋፋ ባለበት በዚህ ወቅት የወያኔው ባለስልጣን አዲሱ ለገሰ ከመንግስት ቁጥጥር ውጭ አልወጣም በማለት መግለጫ በመስጠቱ የሀገሪቱዋን ዜጎች ማበሳጨቱ ታወቀ።

ሐሙስ ሰኔ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. በተወካዮች ምክር ቤት ተብዬው ባቀረበው ሪፖርት ላይ እንደገለፀው «በአሁን ሰዓት ተፈጠረ የተባለው ረሀብ ከመንግስት ቁጥጥር ውጪ አልወጣም። ይህንን የሚያናፍሱት በቅርቡ ሕግ ተረቅቆ ሊፀድቅ የተዘጋጀባቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ለጋሽ ድርጅቶች ናቸው» ሲል አሳፋሪና አሳዛኝ ማብራሪያ ሰጥቷል።

ከጊዜ ወደ ጊዜ በወያኔ ላይ የተጀመረው ተቃውሞ ወደ ትጥቅ ትግል ተቀይሮ ዙሪያውን በጥይት አሩር እየተለበለበ ያለው ወያኔ ሰሞኑን በጅቡቲ መስመር ከፍተኛ ጉዳት እንደደረሰበት ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገለፀ።

ከሁለት ሳምንት በፊት የተጀመረው ይኸው ጥቃት በአፋርና በኢሳ ጐሣዎች መካከል ግጭቱ ይነሳ እንጂ ሁለቱም ወገኖች ፊታቸውን መልሰው በወያኔ ጦር ላይ ጥቃት እንደሰነዘሩበትና ከፍተኛ ኪሣራ እንደደረሰበት በስፍራው የነበሩ የአይን እማኞች ገለፀዋል።

ሁለቱ ጐሣዎች ድሮም ጀምሮ በግጦሽ ቦታ ለኔ ይገባኛል በሚልና በሌሎችም ምክንያቶች እርስ በእርስ የሚጋጩ ሲሆን አሁንም ሰሞኑን የተቀሰቀሰው ግጭት አንደኛው ጐሣ የአንደኛውን ፍየሎችና የቀንድ ከብቶችን ነድተው በመውሰዳቸው መሆኑን የገለፁት ምንጮች በኋላ መልኩን ቀይሮ በአካቢው ሠላም አሰፍናለሁ ብሎ በሰፈረው የፌዴራል ፖሊስ ላይ ሁለቱም ጥቃት መሰንዘራቸውን አስረድተዋል::

የሀገሪቱ ዋነኛ የባህር በር የሆነው ጅቡቲ በቀን በመቶዎች የሚቆጠሩ የከባድ ጭነት ተሽከርካሪዎች መንቀሳቀሻ በመሆኑ በወቅቱ ግጭቱ በተነሳ ጊዜ በደረሱ አሽከርካሪና ረዳት ላይ ጉዳት የደረሰ ሲሆን፣ አንድ ሹፌር ወዲያው ሲሞት በርካታ ረዳቶች ክፉኛ ቆስለው ሆስፒታል መግባታቸውንም የአይን እማኞቹ ገልፀዋል::

የአፋርና የኢሳ ጐሳ ታጣቂዎች በወያኔ ጦር ላይ ድንገተኛ ጥቃት ሰንዝረው በርካታዎቹን ለቁስለኛነት የዳረጓቸው ሲሆን ውጊያው በተካሄደበት አራት ሰዓታት ያህል ከጅቡቲ ወደመኃል የሚያስገባው መስመር ዝግ ሆኖ እንደዋለም እነዚሁ የአይን እማኞች ገልፀዋል::
ወያኔ በፈጠረው ስርዓት አልበኝነት የታጠቁ ኃይሎችም እየተጠቀሙበት ሠላማዊና ንፁኃን ዜጐች ያለምንም ኃጢያታቸው በየመንገዱ እየተገደሉ መሆኑን የገለፁት እነኚሁ የአይን እማኞች አሁንም ሚሌ አካባቢ ጥቃቱ የደረሰባቸው ሹፌሮችና ረዳቶች የዚሁ ሰለባ መሆኑን ሳይሸሽጉ ገልፀዋል::

በአፋርና በኢሳ ተጀምሮ በወያኔ ላይ የተደመደመው ጥቃት አፋሮች ለምን ከብቶቻችን ሲነዱብን ዝም አላችሁ? እያሉ በጥያቄ ሲያጣድፏቸው ኢሳዎች ደግሞ ከኛ ወገን ሰው ሲሞት ምን እርምጃ ወሰዳችሁ? ቆማችሁ ከመመልከት በስተቀር በሚል ሁለቱም በወሰዱት ድንገተኛ ጥቃት በወያኔ ፌዴራል ፖሊሶች ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ አድርሰው መንገዱም ለሰዓታት መዘጋቱን እማኞቹ ገልፀው በአሁን ሰዓት በፍርሀት የተነሳ የተለመደው የመኪና እንቅስቃሴ ቢኖርም ቁጥሩ ግን እጅግ አናሣ መሆኑን ጨምረው ገልፀዋል::

ወያኔ በሁለቱ ጐሣዎች ግጭት ከዳር ሆኖ እሳት ሲሞቅ አስቦ የነበረ ቢሆንም ሳይሳካለት ቀርቶ መልሶ እራሱ ተማግዶ እንደ ጧፍ ሲንቀለቀል መታየቱ ሲያንሰው እንጂ አይበዛበትም ያሉት አንድ የከባድ መኪና አሽከርካሪ በወቅቱ በፈጣሪ ኃይል ተረፍን እንጂ ማንም አልደረሰልንም ይህም ሆን ተብሎ የተደረገ ሴራ ነበር ሲሉ በንዴትና በእህል ይገልፃሉ::

የወያኔ ፌዴራል ፖሊስ ቁስለኞች ወደ አዋሽ አርባ ወታደራዊ ካምፕ የተወሰዱ ሲሆን በርካታ ቁጥር ያለው ሰራዊት ወደ አካባቢው ሰሞኑን ተጓጉዞ መሄዱንም እነዚሁ የአይን እማኞች ገልፀው ወደፊት በእንደዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ሀገሪቷ የምትጠቀምበት የወደብ መስመር ሊዘጋ እንደሚችልና እነ ወያኔም ችግር ውስጥ ሊዘፈቁ እንደሚችሉ ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል::

ከሰኔ 6 ቀን 2000 ዓ.ም በፊት የጀመረው ይኸው ጥቃት ለጊዜው ጋብ ያለ ቢመስልም ያለው ሁኔታ ግን እጅግ አስጊ ነው በማለት ስጋታቸውን የሚገልፁት የከባድ መኪና አሽከርካሪዎች ዋስትና በሌለን ሁኔታ ቤተሰቦቻችንን ለማስተዳደር ስንል ብቻ ለመስራት ተገደናል ሲሉ ቅሬታ እየተሰማቸው ገልፀዋል።

ገንዘብ እንደጣኦት የሚያመልከው ወያኔ ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚደርስበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ኪሣራ የተነሳ እንደ ገደል ላይ ዛፍ ከወዲያ ወዲህ እየተወዛወዘ ምን ማድረግ እንዳለበት እንኩዋን ተቸግሮ ባለበት ወቅት በሀገሪቷ ውስጥ ዘረፋና ግድያ እየተስፋፋ መምጣቱ ታወቀ።

ወያኔ እራሱ በፈጠረው ችግር የተነሳ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስራ አጥነት በሀገሪቱ እየተስፋፋ፣ የኑሮ ውድነት ነግሶ አሁን ደግሞ ከ1977 ዓ.ም ድርቅ እጅግ በባሰ መልኩ ረሀብ የሀገሪቷን ዜጐች እንደቅጠል እያረገፈ ከመሆኑም በተጨማሪ የዕለት ጉርስ ፍለጋ አንዱ አንዱን ወደ መግደል እየተሸጋገረ መሆኑ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚደርሱን ዘገባዎች አስረድተዋል።

በቅርቡ በጐጃም መስመር ከባድ መኪና አስቁመው ዝርፊያ ካከናወኑ በኋላ ማንነታችንን ልታጋልጡ ትችላላችሁ ብለው አሽከርካሪውን ጨምሮ ሌሎች ሶስት ነጋዴዎች ላይ ግድያ የተፈፀመባቸው መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ እዚሁ መዲናይቱ ውስጥ በቀን በጠራራ ፀኃይ ቅሚያና ዝርፊያ እየተካሄደ ሲሆን ዘራፊዎቹ በአብዛኛው የወያኔ መደበኛ ፖሊሶች መሆናቸውንም ዘገባው አብራርቷል።

ይህን የመሰለ የተዝረከረከ እና ስርዓት አልበኝነት የፈጠረው ወያኔ አሁን ደግሞ በቅርቡ ተግባራዊ የሚሆን አዲስ አቅድ አውጥቶ ነባር የመንግስት ሠራተኞችን ሊያባርር ዝግጅቱን ማጠናቀቁን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች የተገኘው ጥቆማ ያስረዳል።

ከመጋቢት 2000 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ታቅዶ የነበረው ይኸው 20 ለአርባ የተባለው አዲስ የማባረሪያ ስልት በወቅቱ ሁኔታዎች ያልተመቻቹላቸው በመሆኑ ለጊዜው ትተውት የነበረ ቢሆንም አሁን ግን ከሐምሌ ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት እያሳደረ መሆኑን ከየመስሪ ቤቱ የሚወጡ ጥቆማዎች ያስረዳሉ።

በቅርቡ ተግባራዊ ይደረጋል የተባለው አዲሱ የማባረሪያ ስልት 20 ዓመት ያገለገለና 40 ዓመት እድሜ ያለው በሚል ሲሆን በተለይ የአዲስ አበባ ጤና ቢሮ ይህንን ቀድሞ ተግባራዊ ለማድረግ እየተጣደፈ እንደሚገኝ ለቢሮው ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል።

ከ20 ዓመት ጀምሮ በተላላኪነትና በፅዳት ሰራተኝነት በጥበቃነት አልፎ ተርፎም በመዝገብ ቤት ሠራተኝነትና በመሳሰሉት ስራ ላይ የተሰማሩ የሀገሪቱ ዜጐች የአይናችሁ ቀለም አለማረንም ተብለው ቅነሳ ሊደረግባቸው መሆኑ በእጅጉ አሳዛኝና አሳፋሪ ከመሆኑም በላይ ወያኔ ለሀገሪቱ ሕዝቦች ያለውን ንቀትና ጥላቻ ያሳያል ሲሉ አንድ የሚኒልክ ሆስፒታል ጥበቃ ሰራተኛ ሲገልፁ ተደምጠዋል።

እንኩዋንስ ዘንቦብሽ እንዲያውም ጤዛ ነሽ እንዲሉ ከ300 ብር በላይ ባልዘለለው ደመወዝ ተብዬ ከ20 ዓመት በላይ በጥበቃ ስራ ላይ ተሰማርተን እያገለገልን ያለን ሰዎች በኑሮ መወደድ ሳቢያ በቀን አንዴ እንኩዋን ቤተሰቦቻችንን ማብላት ተስኖን እያለ ወያኔ አሁን ደግሞ የበለጠ በችግር ውስጥ እንድንዘፈቅ ከስራ ሊያባርረን ማሰቡ ህሊና ያልፈጠረባቸው የተጠራቀሙበት ቡድን መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል ሲሉ ሀዘንና ምሬት በተቀላቀለበት ሁኔታ ሲገለፁ ተደምጠዋል::

ዛሬ የአንድ ኩንታል በቆሎ ከ600 ብር በላይ ባሽቀበበትና አንድ ኩንታል ስንዴ ወደ 800 ብር እየሮጠ ባለበት ወቅት ጤፍ ወደ 1300 ብር እየተንጠራራ ባለበት በዚህ ወቅት ባለችን 300 ብር በማትሞላ ብር ከቤተሰቦቻችንን ጋር እንዳንቃመስ ይባስ ብለው አይናችሁን አንይ በማለት የግፎች ሁሉ ግፍ ወያኔዎች ሊፈፅሙብን መዘጋጀታቸው እጅግ ሰብአዊነት የሌለው በሕይወት እንዳንኖር ሆን ተብሎ ታቅዶ የተሰራ ነው ሲሉም እነዚሁ ወገኖች እያለቀሱ ይገልፃሉ::

የወያኔ ስርዓት በህዝብና በሀገር ላይ የሚሰራው ደባና ተንኮል የተነሳ የራሴ ናቸው የሚላቸው አባላቱና ከፍተኛ ባለሥልጣናቱ እየከዱት መኮብለላቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እየተበራከተ እንደሚገኝ ከሚደርሱን ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል::

ከአንድ ሳምንት በፊት ወደ እንግሊዝ ከተጓዙት 6 የወያኔ ካድሬዎች መካከል ሁለቱ በዚያው ማቅረታቸውንና ጥገኝነት መጠየቃቸውን ከምክር ቤት ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

የተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ሠራተኞችና የመምሪያ ኃላፊ የሆኑት አቶ ምህረተአብ ገብረ ሕይወት እና አቶ ሹመቴ መንግስቱ የተባሉት ሁለቱ የወያኔ ባለሥልጣናት በእንግሊዝ ቢፒአር ጥናት ለማድረግ ተልከው በሄዱበት በዚያው መቅረታቸውን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ምህረተአብ ገብረሕይወት የውስጥ ኦዲትና ኢንስፔክሽን ኃላፊ የሕወሓት አባል ሲሆን፣ ሹመቴ መንግስቴ ደግሞ የተወካዮች ምክር ቤት አባሎች ጉዳይ ኀላፊና የቤቶች ተቆጣጣሪ የብአዴን አባል መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ ስርዓቱ እድሜው አጭር መሆኑን ቀድመው በመረዳታቸው እራሳቸውን ለማዳን የወሰዱት እርምጃ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

የወያኔ ስርዓት በህዝብ ላይ በሚሰራው ግፍና በደል የተነሳ ቀኝ እጄ ናቸው የሚላቸው ካድሬዎቹ ሳይቀር እየከዱትና እየሸሹት መሆኑ ስርዓቱ ከየትኛውም አቅጣጫ ድጋፍ የሌለው መሆኑን አመላካች ነው የሚሉት ምንጮች በቅርቡ ለስራ ተጉዞ የነበረው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ፕሬዝዳንት የፕሮቶኮል ኃላፊ አቶ ቴዎድሮስ ማሞ አውስትራሊያ ሄዶ መቅረቱም የዚሁ አካል ነው ሲሉም ገልፀዋል::

በተጨማሪም በወያኔ ግፍና በደል ተማርረው ወደ ውጭ ሀገር የተሰደዱ የጋምቤላ ክልል ተወላጆችን ለመመለስ የጋምቤላ ክልል ፕሬዝዳንትን ጨምሮ አንድ ልዑካን ቡድን ወደ አሜሪካና ካናዳ ተልኮ የነበረ ሲሆን፣ ቡድኑ የተላከበትን ሳያሳካ የተመለሰ መሆኑ ሲታወቅ ከልዑካን ቡድኑ መካከል አንድ ኢንጅነር ስርዓቱን ከድቶ በአሜሪካ ጥገኝነት መጠየቁ ታውቋል።

ቀንደኛው የወያኔ ካድሬና የጋምቤላ ክልል ከፍተኛ ባለስልጣን የነበረው ኢንጅነር ኦቦንግ የተባለው ስርዓቱ በአሁን ሰዓት በሕዝቦች በሚያደርሰው በደልና ግፍ የተነሳ አብሮ ለመጓዝ እንደሚቸገር ገልፆ አሜሪካ ውስጥ በተዘጋጀ በአንድ መድረክ ላይ በጋምቤላ ክልል ተወላጆች ላይ በአሁን ሰዓት እየተወሰደ ያለው እርምጃን አስመልክቶ ይፋ በማድረጉ ወያኔ ሊገለኝ ይችላል በሚል ፍርሀት ስርዓቱን ከድቶ ጥገኝነት መጠየቁ ታውቋል።

የመለስ ዜናዊ ሎሌ ሆነው የአማራውን ህዝብ ለወያኔ ተገዢ ለማድረግ በተለጣፊነትና ከሀዲነት ሲያገለግል የቆዩትና ራሳቸውን ብአዴን ብለው የሚጠሩት ቡድን አንዱ መሪ የሆነው ህላወ ዮሴፍ በአሁኑ ጊዜ በዋሺንግተን ከተማ እንደሚገኝና በገንዘብ ድጋፍ ለመግዛትም እየተሯሯጠ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ህላዌ ዮሴፍና አጀቦቹ በሌሎች ከተማዎችም ሲዘዋወሩ ቆይተዋል። በተቃውሞ ሰልፍ አለመዋከባቸው ደግሞ የኢትዮጵያውያኖችን እንቅስቃሴና ድርጅታዊ ይዘት መዳከም ገላጭ ነውም ተብሏል። ህላዌ ዮሰፍ የኢትዮጵያ መሬት ለሱዳን አልተሰጠም ብሎ እየካደ በዚያው አፉ ደግሞ ሱዳን ያሰራቸውን ወያኔ አስለቀቀ ብሎ ሊመፃደቅ ሲሞክር ተደምጧል። ገንዘብ ሞልቶናልና እንሰጣለን እናበድራለንና ኑ ወደ ሀገር ግቡ ነግዱ ቤት ግዙ እያለ ሰበካውን የተያያዘው ህላዌ በወ.ጨ. ሀገር ያለውን ኢትዮጵያዊ በሆዱ እገዛዋለሁ የሚለውን የወያኔ ፖለቲካ በሰ.ራ ሊያውል እየጣረ ነው ተብሏል። በተያያዘ ዜና ደግሞ የሱዳኒ./ ወታደር በቋራና መተማ ገፅ አሁንም በአርሶ አደሮች ላይ ጥቃት እያደረሰ ሲሆን አርሶ አደሩ ባለው አቀም የመከላከል እርምጃ መጀመሩም ተዘግቧል። ባባዕድ ሀገር በተለይ በአመሪካ ተቋቋመ የተባለው የድንበር ጉዳይ ኮሚቴም በወያኔ ሰርጎ ገቦች የተያዘ በመሆኑ በሚገባ ሊንቀሳቀስ ካለመቻሉ ሌላ በተጨባጭ ሊታገል ለተነሳው ሕዝብ እየደረሰለት አለመሆኑ ተዘግቧል።

በመጨሻም ወያኔ እራሱ ባደራጀው ታጣቂ ቡድን በወለጋ ውስጥ ዘግናኝ ጭፍጨፋ ያደረገ ሲሆን ከእነዚህ ሟቾች መካከል የ55 ሰዎች ስም ዝርዝር እጃችን ገብቷል።

ወያኔ በሕዝቦች ላይ ባለው ጥላቻና ተቃዋሚዎች ይንቀሳቀሱበታል በሚል ፍራቻ የተነሳ አንደ መሬት እየቆረሰ ለበአድ ሲሰጥ ሌላ ጊዜ ደግሞ የታጠቀ ኃይል አስርጐ በማስገባት ዜጐችን እያስጨፈጨፈ ይገኛል።

በቅርበ በወለጋ ውስጥ በበርካታ ዜጎች ላይ ጭፍጨፋ ያካሄደ ሲሆን በወቅቱ ከ130 በላይ ሰዎች እንደተገደሉ መዘገባችን አይዘነጋም፡፡ ከእነዚህም መካከል የ55 ሟቾች ስም ዝርዝር እንደሚከተለው ነው :-

1. ኩመራ ደሬሣ
2. ተስፋዬ ቀነአ
3. አስማረ ቸኮል
4. ታደሰ ድሪብሣ
5. አብዲ መስፍን
6. ተረፈ ነገሪ
7. ከበደ ገለታ
8. ፍቃዱ ኦልቀባ
9. ፍቃዱ ሳልባና
10. ሳልባና ገለታ
11. ተስፋዬ አስረስ
12. ኪዳኑ
13. ፈይሳ ወዳጆ
14. ኢረና ጂልቻ
15. ደረሰ ሽፈራው
16. ለማ ኦሊ
17. ብርሀኑ ዳርጌ
18. ስንታሁ ምትኩ
19. ሣሙኤል ተመስገን
20. ተመስገን ኦልፋዳ
21. ኢፋ አሰፋ
22. ከድር ጀማል
23. ቡሻ ደባ
24. ዩሐንስ መኮንን
25. ዋቅጋሪ ደሬሳ
26. ሞይሳ በዳሣ
27. ዋቅሹም
28. ተስፋዬ መንገሻ
29. ከድር ዩያ
30. ኃይሉ መታፈሪያ
31. ቦጋለ ዋቅቶሌ
32. ዳባ ጉዲና

33. አቡሻ ሰቦቃ
34. ምትኩ ያደታ
35. ፎሎ ቡልቲ
36. ተስፋ አዎታ
37. ከበደ ፉፋ
38. አባ ኪሴ
39. ኦላኒ
40. ሰለሞን ዋና
41. ዳንኤል ደፋ
42. ናስር ቀነኒ
43. ታመነ
44. ጌታሁን አንዳለ
45. ደገፉ ገመዳ
46. ዘለቀ ሆርዶፋ
47. ገዋ
48. አመኑ
49. ሁሴን ሰኢድ
50. ተስፋዬ
51. ኢታና ዋቅጅራ
52. ተስፋዬ ታፈሰ
53. ተረፈ ዋቅቶሌ
54. ጉርሙ ዋቅቶሌ
55. ግርማ ረጋሳ ናቸው፡፡

<u>ማስታወሻ፡-</u>

- በዝዋይ እስር ቤት ላሉ እስረኞች የምግብ አቅርቦት በሁለት ቀን አንዴ እንደሆነ፣
- ምግብ ተብሎ የሚቀርብላቸውም ቢሆን የበቆሎ መጠኑ ያነሰ ቂጣ መሆኑን፣
- በምግብ እጥረት በርካታ እስረኞች ለበሽታ እየተዳረጉ መሆኑን፣
- የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የተባሉት ባለሥልጣናት ስብሰባ በሚል በቀን በሺዎች የሚቆጠር ገንዘብ ተመድቦላቸው እየመዘበሩ መሆኑን፣
- በተመሳሳይም በናዝሬት እስር ቤት የምግብ እጥረት ተከስቶ በርካቶች ለበሽታ መዳረጋቸውን፣

- ከጥቂት ቀናት በኋላም እስረኞች ሊመገቡ የሚችሉት ምግብ እንደሌለ የእስር ቤት ምንጮች መግለፃቸው"፣

- የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በረሐብ እየተቆሉ መሆናቸውን፣

- ለአንድ ተማሪ በቀን መጠኑ ያነሰ ሁለት ዳቦ ከአንድ ማንኪያ ሽሮ ጋር ብቻ እንደሚሰጣቸው፣ የዲላ ዩኒቨርስቲ እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ተመሳሳይ ችግር ውስጥ እንዳሉ፣

- የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና የአራት ኪሎ የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎችም የዚሁ ሰለባ መሆናቸውን ከምንጮቻችን ያገኘነው መረጃ ያረጋግጣል፡፡